# ነገ ኢሕአዴግን ልንደግፍ እንችላለን !

ግርማ ካሳ (ቺካጎ)
muziky68@yahoo.com

ኅምሌ 30 2000

የቅንጅት ወራሽ ነዉ ብዬ የማምነዉ ፣ መሰረቱን ኢትዮጵያ ያደረገዉንና ሰላማዊ በሆነ መንገድ በኢትዮጵያ ዉስጥ ለዉጥ ለማምጣት እየታገለ ያለዉን አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ እንደ አብዛኛዉ ኢትዮጵያዊ እደግፋለሁኝ። እንደ አብዛኛዉ ኢትዮጵያዊም ኢሕአዴግን የምቃወም ሰዉ ነኝ።

ኢሕአዴግን የምቃወመዉ በኢሕአዴግ ዉስጥ ያሉ ግለሰቦች ላይ የግል ችግር ወይንም ጥላቻ ስላለኝ እንዳልሆነ ሁሉ ፣ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲንም ስደግፍ በአመራር ላይ ያሉ ሰዎችን በግለሰብ ደረጃ ስለምደግፋቸዉ አይደለም ፓርቲያቸዉን የምደግፈዉ።

ኢሕአዴግን የተቃወምኩት ኢሕአዴግ የሚያራምዳቸዉ አንዳንድ ፖሊሲዎች ስለማይስማሙኝና ላለፉት አሥራ ሰባት አመታት አገርን የሚጎዱ ትላላቅ ስህተቶች በኢሕአዴግ ተሰርተዋል ብዬ ስለማምን ነዉ። የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲን የምደግፈዉ ደግሞ ይዟቸዉ በተነሳቸዉ መርህዎችና በኢትዮጵያዊነት ላይ ባለዉ የማያሻማ አቋሙ ነዉ።

እንግዲህ ኢሕአዴግን መቃወሜና አንድነትን መደገፌ እንዳለ ሆኖ፣ ከተለየ ማዕዘን አንድ ቁም ነገር ለአንባቢያን ማካፈል እፈልጋለሁኝ። ይህም ኢሕአዴግ በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ስርዓት የበለጠ እንዲሰፍን ሊኖረዉና ሊጫወተዉ ስለሚችለዉ ሚና ነዉ።

በደቡብ አፍሪካ ያየነዉ በኢትዮጵያ እንዳይደገም በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ እንዲኖር **ኢሕአዴግ ጠንካራ ፓርቲ ሆኖ መቀጠል አለበት ብዬ አስባለሁ።**

በቅርቡ ደቡብ አፍሪካዊያን፣ የዉጭ አገር ዜጎች ከአገራቸዉ እንዲወጡ የተለያዩ አላስፈላጊ እንቅስቃሴዎችን እንዳደረጉ በሰፊዉ ተዘግቧል። ይህ የሆነዉ፣ ደቡብ አፍሪካዉያን በሌሎች አፍሪካ አገር ነዋሪዎች ላይ ችግር ኖሮዋቸዉ ሳይሆን የአፓርታይድ አገዛዝ በምርጫ ከተወገደ ጊዜ አንስቶ፣ ስልጣን የያዘዉ ኤኤንሲ፣ የሕዝቡን ኑሮ አለማሻሻሉና የሕዝቡ የድህነት መቀጠል ያመጣዉ ጣጣ ነዉ። ደቡብ አፍሪካዉያን ከኤኤንሲ ዉጭ ሌላ አማራጭ አላገኙም። ስለዚህም ብሶታቸዉን በሌላ መልኩ የገለጹበት ሁኔታ የተፈጠረ ይመስለኛል።

እንደዚሁም ኢሕአደግ እንደገና ማንሰራራት እሲያቅተዉ ድረስ በምርጫ ተሸንፎ፣ እንበል አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ የኢትዮጵያ ኤኤንሲ ቢሆን፣ እንደ ደቡብ አፍሪካ አንድ ፓርቲ ብቻ አይሎ ሊወጣ ይችላል። በምርጫ ሊሸነፍ ቢችልም ኢሕአዴግ ጠንካራ ፓርቲ ሆኖ እንዲቀጥል ከተደረገ ግን፣ ኢሕአዴግን ተከቶ የሚመጣዉ ማንኛዉም ፓርቲ ለሕዝብ የገባዉን ቃል ካልጠበቀ በ2007 ዓ.ም እንደገና በምርጫ የሚነሳበት ሁኔታ ማመቻቸት ይቻላል።

ኢሕአደግ አንድ ነገር ጠንቅቆ ማወቅ አለበት እላለሁኝ፤ በጠመንጃ ኃይል መመካት ዘለቄታዊ መፍትሄ እንደማያመጣለት ። ፓርቲዉን አይጠቅምም፤ አገሪቷንም አይጠቅምም። ስለዚህ **ኢሕአዴግ ወደፊት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ዉስጥ ሚና እንዲኖረዉ ካስፈለገ በጠመንጃ ጉልበት ላይ ብቻ የተመሰረተ ኃይል ይዞ ከመቀጠል ይልቅ በሕዝብ ድጋፍ ላይ የተመሰረተ ጉልበት ሊኖረዉ የሚችልበትን ሁኔታ ከአሁኑ ማመቻቸት አለበት።** ለዚህም እንዲረዱ ይጠቅማሉ ብዬ የማስባቸዉን የመፍትሄ ሃሰቦችን በአክብሮት ከታች ለመዘርዘር እሞክራለሁን።

አንዳንዶች ኢሕአዴግ ምንም ጥሩ ነገር እንዳልሰራ አድርገዉ የሚቆጥሩ ባይጠፉም ኢሕአዴግ በአገራችን ኢትዮጵያ ያመጣቸዉ የማያከራክሩ በርካታ አዎንታዊ ለዉጦች እንዳሉ የማይካድ ነዉ። ለምሳሌ በደርግ ጊዜ የነበረዉን አስከፊ ገጽታ ብናስታዉስዉና ከዚያን ወቅት ጋር አሁን ያለዉን ሁኔታ ብናወዳድረዉ ተጨባጭ የሆኑ ክንዋኔዎችን እናያለን።

- ወደ ዉጭ አገር ለመዉጣት ከኤምባሲዎች ቪዛ ከማግኘት የበለጠ የኢትዮጵያ ፓስፖርት ማዉጣት በጣም ይከብድ ነበር። ትዝ ይለኛል የመጀመሪያ ቀዩን የኢትዮጵያ ፓስፖርት ሳወጣ። ከቀበሌያችን አኢወማ (የአብዮታዊ ኢትዮጵያ ወጣቶች ማህበር) ወረቀት ማጻፍ ነበረብኝ። የአኢወማዉ ሊቀመንበር ከጠመመ ፓስፖርት የማዉጣቱን ጉዳይ እርሱት። ከዚያ ወታደራዊ ኮሚሳሪያት ወደ ሚባል፣ ጎላ ሚካኤል አካባቢ ወደ ሚገኝ ጽ/ቤት ይኬዳል። ለብሄራዊ ዉትድርና ተፈልጎ የነበረ ሰዉ ከሆነ ለመዉጣት ፈቃድ አይሰጠዉ። ይህን የመሳሰሉ ብዙ አፈናዎች በደርግ ጊዜ እንደነበሩ ይታወሳል።

  አሁን አለአንዳች ቢሮክራሲ ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ፓስፖርት ማግኘት ሲችል እንደፈለገ ከአገሩ መዉጣት ወደ አገሩ መመለስ የሚችልበት ዘመን ነዉ። ይህ የኢሕአዴግ ዉጤት ነዉ።

- በኢትዮጵያ የተለያዩ ግድቦች፣ መንገዶች ፣ ክሊኒኮች፣

ትምህርት ቤቶችና ፎቆች እየተሰሩ ነዉ። ከአዲስ አበባ ድሬደዋ በስድስት ሰዓት፤ ከአዲስ አበባ ደብረ ማርቆስ በአምስት ሰዓት ይገባል። በሳሞራ(አፋር ክልል) ፣ በጅጅጋ (ሱማሌ ክልል) ፣ በመቀሌ ..እንዲሁም በተለያዩ የአገራችን ግዛቶች በርካታ ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች ተመስርተዋል። ትልቅ የልማት እንቃቃሴዎች እየታዩ ነዉ። እነዚህ ሁሉ የኢሕአዴግ ዉጤቶች ናቸዉ።

- ከዚህ በፊት በአገራችን ያልታየ ተጨባጭ የሆኑ አንጻራዊ የዲሞክራሲ ለዉጦች አይተናል። ከምርጫ ዘጠና ሰባት በፊት እንደ አስኳል፤ ኃዳር ፣ ሚሊሊከና ነጻነት የመሳሰሉ ለዲሞክራሲ እንቅስቃሴ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረጉ በርካታ ጋዜጦች በነጻነት ይታተሙ ነበር። ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኃላ እነዚህ ጋዜጦች ተዘግተዉ በርካታ ጋዜጠኞች መታሰራቸዉ ቢታወስም፣ በአሁኑ ሰዓት ኢሕአዴግ ካለፈዉ ስህተት ተምሮ፣ ተዘግተዉ የነበሩ ነጻ ጋዜጦች እንደገና እንዲያብቡ እያደረገ ያለ ይመስላል። እምቢልታ፣ አዉራምብ ታይምስ፣ አዲስ ነገር፣ ነጋድራስና እንደምሳሌ መጥቀስ እንችላለን። ይህም ወደቀናዉ መንገድ የሚደረግ ትልቅ እርምጃ ሲሆን የኢሕአዴግ ወጤት አድርጌ ነዉ የማየዉ።

- በደርግ ጊዜ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዉያን በረሃብ አልቀዋል። በአጼ ኃይለስላሴም ጊዜ እንደዚሁ። በኢሕአዴግ ያኔ እንደታየዉ አስከፊ ረሃብ አልታየም። ድርቅ ወይንም የዝናብ እጦት ሳይኖር ቀርቶ አይደለም። ነገር ግን ኢሕአዴግ የዘረጋዉ ሞኒተሪንግ ሲስተም ትልቅ አስተዋጾ እንዳደረገ ብዙዎች ይናገራሉ። ረሃብና ድርቅ በተከሰተባቸዉ ቦታዎችም አስቸኳይ እርምጃ በመዉሰዱ ላይ ኢሕአዴግ ከዚህ በፊት ከነበሩ አገዛዞች እጅግ በጣም የተሻለ ሆኖ ነዉ የሚገኘዉ።

  በአገራችን የረሃብ ችግር የለም ማለት አይደለም። በቅርቡ በሻሸመኔ አካባቢ ያየነዉ አሳዛኝ ሁኔታ ረሃብና ችጋር የአገራችን ቀንደኛ ጠላት እንደሆኑ ያሳያል። ይህን ጠላት ኢሕአዴግ ብቻ ሳይሆን ሁላችንም ልንዋጋዉ የሚገባ፣ ሁላችንም ሃላፊነት ልንወስድበት የሚገባ አገራዊ ጉዳይ ነዉ።

ከላይ የዘረዘርኳቸዉና ሌሎች በርካታ ኢሕአደግ ያስመዘገባቸዉ፣ በአንጻራዊነት መልካም የሚባሉ ዉጤቶች እያሉም ኢሕአዴግ እንደሚገባዉ የሕዝብን ድጋፍ ያገኘ አይምሰልም። በሕዝብና በኢሕአዴግ መካከል ያለዉ ግንኙነት ላይ ትልቅ ችግር ያለ ይመስላል።

እኔ የኢሕአደግ ባለሥልጣን ብሆን « ይህን ሁሉ ልማት አምጥተን ለምንድን ነዉ ህዝቡ የማይደግፈን? » የሚለዉን ትልቅ ጥያቄ ጠይቄ መልስ ለማግኘት እሞክር ነበር።

አንዳንድ የኢሕአዴግ ጭፍን ደጋፊዎች «ኢሕአዴግ በሕዝብ ይደገፋል» ብለዉ ለመከራከር ይሞክራሉ። ነገር ግን እራሳችንን አናሞኝና እራሳቸዉ የኢሕአደግ ባለሥልጣናት ኢሕአዴግ በሕዝብ የሚደገፍ እንዳልሆነ ያዉቃሉ። ነጻና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ቢደረግ በትግራይ ክልል ዉስጥ ሳይቀር እንኳን በዝረራ የሚሸነፍ ድርጅት ነዉ።

**ይልቅስ የሚያዋጣዉ በጠመንጃ ከመታመን ይልቅ « ምን ብናደርግ ነዉ ሕዝቡን ወደኛ ማምጣት የምንችለዉ ?» የሚል ጥያቄ በመጠየቅ የኢሕአዴግ ፖሊት ቢሮ ስር ነቀል የሆኑ ለዉጦችን ማድረግ የሚቻልበትን ሁኔታ ቢዘረጉ ጥሩ ይሆን ነበር።** ግልጽነት የተሞላበት የዉስጥ ግምገማ ተካሂዶ ሕዝብ ሊደግፋቸዉ የሚችሉ አዳዲስ ፖሊሲዎችን አርቅቀዉና በአዲስ መልክ ተደራጅተዉ ቢወጡ በሚቀጥለዉ ምርጫ ማሸነፍ ባይችሉም እንኳን የሽንፈታቸዉን መጠን በእጅጉ ሊቀንሱ ይችላሉ ብዬ አስባለሁኝ። ድንገትም፣ ማን ያዉቃል፣ ሕዝብ የሚደግፋቸዉን ፕሮግራሞች ካነገቡ ነጻና ገለልተኛ በሆነ ምርጫ ሊያሸንፉም ይችሉም ይሆናል።

**ኢትዮጵያን ባህር አልባ መሆኗ !**

ኢሕአዴግ ኤርትራ እንድትገነጠል ወይንም ነጻ እንድትወጣ ማድረጉ ኢትዮጵያን ባህር አልባ አድርጓታል። በዚህም ምክንያት በድፍረት መናገር እችላለሁኝ ኢሕአዴግ ከፈጸማቸዉ ስህተቶች ሁሉ በአንደኛነት የሚቀመጠዉ ስህተት ይሄዉ ነዉ። በዚህ ቢሉ በዚያ ፣ የኢሕአዴግ ባለስልጣናት የኢትዮጵያን ሕዝብ በምንም ረገድ ሊያሳምኑ አይችሉም። አልቻሉምም። ይልቅስ ይህንን ትልቅ ስህተት እንደሰሩ ማመንና መቀበል አለባቸዉ። እንደ ስዊዘርላንድ ያሉ አገራትን በመጥቀስ ለማደግ ወደብ አያስፈልግም የሚል ሕዝብን የሚንቅና መሰረት የሌለዉን ማስተባበያቸዉን ቢያቆሙ መልካም ነዉ።

በድፍረት «ተሳስተናል» ብለዉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ ቢጠይቁ ትልቅነታቸዉን ያሳያሉ። በወቅቱ በነበረዉ ሁኔታ እንደ መንግስት ሳይሆን እንደ ሽምቅ ተዋጊ አስበዉ፣ ለሰላምና ለመረጋጋት ሲሉ እንዲሁም ከኤርትራ መንግስት ጋር ለዝንተ አለም ወዳጅ ሆነዉ የሚኖሩ መስሏቸዉ ኤርትራን እንዳስገነጠሉ እዉነታዉን ለሕዝብ አስረድተዉ መሳሳታቸዉን ቢናገሩ በጣም ይጠቀማሉ እንጂ አይጎዱም፡

እርግጥ ነዉ ለእነርሱ ይህን ማድረግ በጣም ይከብዳል። ስህተትን መቀበል ትልቅ የመንፈስ ብርታትን የሚጠይቅ ጉዳይ ነዉ። «ተሳስተናል፤ አጥፍተናል» ቢሉ በአንዳንዶች

ዘንድ የበለጠ ሊያስከስሳቸዉ ይችላል። ነገር ግን በአብዛኛዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ በእጅጉ ከበሬታ የሚያሰጣቸዉ ድርጊት ነዉ ብዬ አምናለሁኝ። « ተሳስተናል። በተቻለ መጠን ኢትዮጵያ የባህር በር ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲኖራት እናደርጋለን» ብለዉ እንዲነሱ አበረታታቸዋለሁ።

ከኤርትራም ጋር ወደፊት በሚደረግ ዉይይት ለኤርትራ ብዙም ጥቅም የሌለዉን የአሰብ ወደብ ሙሉ ለሙሉ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ የሚደረግበትን ሁኔታ በማመቻቸትና ካስፈለገና ኤርትራዉያን ፈቃደኛ ከሆኑ (ወይንም እንዲሆኑ በማሳመን) ከኢትዮጵያዉያን ወንድሞቻቸዉ ጋር እንደገና በሰላም የሚቀላቀሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ለኢሕአዴግ ትልቅ አበይት ታሪካዊ ክንዋኔ ይሆንለት ነበር።

**ኢሕአዴግ የሚያራምደዉ የዘር ፖለቲካ ነዉ**

ኢትዮጵያ ዉስጥ አገዛዙ ከኢትዮጵያዊነት በላይ ቅድሚያ የሚሰጠዉ ለዘር ነዉ። ማንኛዉም ኢትዮዮዮጵያዊ ዘሩን (ወይም ብሄር ይሉታል ኢሕአዴጎች) መምረጥ አለበት። አማራ፣ ትግሬ፣ ኦሮሞ፣ ጉራጌ ..ወይንም አንድ ብሄር ካልመረጠ መታወቂያ አያገኝም።

በሰሜን ጎንደርና በሰሜን ወሎ ትግሬዉና አማራዉ፤ በአርሲ፣ በሸዋ፣ በጎጃም በኢሊባቡር ...አማራዉን ኦሮሞዉ በወሊሶ ኦሮሞዉና ጉራጌዉ በሲዳሞ ሲዳማዉና ኦሮሞዉ .....ተደባልቋል። ለዘመናት እየተጋባ ሲዛመድና ሲዋለድ የነበረን ሕዝብ እንደገና ለመሰነጣጠቅ የተደረገዉ ሙከራ በሁለተኛነት ኢሕአደግን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ያጣላዉ ጉዳይ ነዉ።

ኢትዮጵያዉያን ዘራቸዉን እንዲመርጡ መገደዳቸዉ ብቻ አይደለም። ለምሳሌ አንድ ወቅት በናዝሬት አዳም የተወለዱ ኢትዮጵያዉያን "ኦሮሞ ነን" ካላሉ በስተቀር መታወቂያ አይሰጣቸዉ ነበር። ይህ የሚያሳየዉ በዘር ላይ ብቻ የተመሰረተ ኢትዮጵያዉያንን የማግለል ፖለቲካ እንደሆነ ነዉ። ይህን ጣጣ ያመጣዉ ኢሕአዴግ ነዉ።

ስለዚህ በዚህ አንጻር የኢሕአዴግ መሪዎች ማሻሻያ በአስቸኳይ ማድረግ አለባቸዉ ብዬ አስባለሁኝ። ማሻሻያዎችን ካላደረጉ ግን ከሕዝብ ጋር ተጣልተዉ እንደሚቀጥሉ ማወቅ አለባቸዉ። በምርጫ ዘጠኛ ሰባት የኢትዮጵያ ህዝብ ቅንጅትን ሲመርጥ የቅንጅት መሪዎችን ጥንካሬ ስላየ አልነበረም። ነገር ግን ኢሕአዴግ ለአሥራ አራት አመታት ሲያራምደዉ የነበረዉን የዘር ፖለቲካ «አልፈልግም» ብሎ ኢትዮጵያዊነትን ለማረጋገጥ ስለፈለገ እንጂ። በዘጠና እባት የኢትዮጵያ ህዝብ የመረጠዉ «ኢትዮጵያዊነትን" ነዉ።

የኢሕአዴግ የቅርብ አማካሪ የነበሩና ስለ ኢትዮጵያ ጉዳይ ሰፋ ያለ ግንዛቤ ያላቸዉ ሚስተር ፖል ሄንዚ በቅርቡ በጻፉት ጽሁፍ ላይ ኢሕአዴግ አሁን ያለዉን የኢትዮጵያ ግንዛቤ ከግምት ዉስጥ በማስገባት በአዲስ መልክ እንዲደራጅ ጠይቀዋል። ኢሕአዴግ እንደዉም ስሙን ሁሉ ቀይሮ በአዲስ ሁኔታ የኢትዮጵያን አንድነትና ሉዓላዊነትን በማስጠበቅ ላይ ያተኮረና ከ"ዘር ፖለቲካ" በራቀ መልኩ መንቀሳቀስ ቢችል መልካም እንደሆነ ነዉ እኚህ ሰዉ የጠቆሙት። እንደዉም የአዲሱ የኢሕአዴግ ፓርቲ ስም "የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ" ሊሆን እንደሚችልም ጽፈዋል።[1]

ስም መቀየሩ «ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም» እንደሚባለዉ ስለሆነ ግድ የለም ኢሕአዴግ ስሙን ይዞ ቢቀጥል ችግር የለዉም። ነገር ግን የሚስተር ሄንዝን ምክርን በሰፊዉ እጋራለሁ። ኢሕአዴግ የሕዝብን ፍላጎት መገንዘብና እራሱን በህዝብ ፍላጎት አንጻር ማደራጀት አለበት እላለሁኝ።

የሕዝብ ፍላጎት ደግሞ አንድነት እንጂ መከፋፈል አይደለም። ስለዚህ ኢሕአደግ በዚህ ረገድ ተጨባጭ የሆነ እርምጃዎችን ማድረግ ይጠበቅበታል። ሊወሰዱ ይጠቅማሉ ከምላቸዉ እርምጃዎች መካከል እስከ መገንጠል የሚለዉን አንቀጽ ከሕገ መንግስቱ እንዲነሳ ማደረግና በዘር ወይንም ቋንቋ ላይ ብቻ የተመሰረተ ፌዴራሊዝምን በተሻለ፣ ቋንቋን ጂኦግራፊን ኢኮኖሚንና የሕዝብን ፍላጎት ባካተተ በአዲስ ፌዴራሊዝም መተካቱ ይገኙበታል።

**የዲሞክራሲ ተቋማትን መገንባት**

አብዛኞቻችን እንደምናወቀዉ በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ተቋማት እምብዛም የጠነከሩ አይደለም። ፍርድ ቤቶች፣ ምርጫ ቦርዱ፣ የሕዝብ የመገናኛ ብዙሃን ነጻና ገለልተኛ አይደሉም። የፖሊስና የደህንነት አባላት እንዲሁም የኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት ከፍተኛ መኮንኖች አብዛኞቹ አገርን ሳይሆን ኢሕአደግን ነዉ የሚያገለግሉት።

ኢሕአዴግ እነዚህን ተቋማት በመቆጣጠሩ ጊዚያዊ ጥቅም አግኝቶ ይሆናል። ነገር ግን ይህ ጊዚያዊ ጥቅም ዘለቄታዊ ጉዳት ለድርጅቱ ለራሱ የሚያመጣ ነዉ። እነዚህ ተቋማት የአንድ ፓርቲን ጥቅም አስጠባቂ ሆነዉ ከታዩ የዲሞክራሲ

---

[1] http://smgebru.blogspot.com/2008/06/ethiopia-henzes-views-on-eprdf.html

ስርዓት ግንባታዉ በእጅጉ ይጎዳል። ኢሕአደግም ለሕዝብ ጥቅምና መብት እንደቆመ ሳይሆን አምባገገን እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል። አምባገነኖችን ደግሞ እንኳን የሰዉ ልጆች እንሥሣዎችም አይፈልጓቸዉም።

ኢሕአደግ በዚህ ረገድ ትልቅ ማስተካከያ ማድረጉ በሶስተኛነት የሚመደብ ቁልፍ ጉዳይ ነዉ።

- የምርጫ ቦርድ ነጻና ገለልተኛ እንዲሆን መደረግ አለበት። በየክልሉ ያሉ የቀበሌና የደህንነት አባላት ሰፊ ስልጠና እንዲሰጣቸዉና የዜጎችን የመደራጀት የዲሞክራሲያዊ መብት የሚጋፋ የክልል ባለስልጣን በሕግ ፊት ተጠያቂ እንደሚሆን ኢሕአደግ በተጨባጭ ሁኔታ ማሳየት ይጠበቅበታል።

- የኢትዮጵያ ቴሌቭዥንና ሬዲዮ በደርግ ዘመን እንደነበረዉ የገዢዉ ፓርቲ ርካሽ ፕሮፓጋንዳ መሳሪያ ከመሆን ይልቅ ለሕዝብ ጥቅም የቆሙ በበላሞያዎች የተሞሉ በገለልተኛ ቦርድ የሚተዳደሩ ቢሆኑ ለኢሕአዴግም ለኢትዮጵያም ትልቅ ጥቅም ያመጣሉ።

  አሁን እየተስፋፋ ያለዉ የነጻ ፕሬስ አበራታች ቢሆንም በጋዜጠኞች ላይ የሚደርሰዉ እንግልት መቆም አለበት። የአዉራማባ ታይምስ ዋና አዘጋጅ አቶ ዳዊት ከበደ፣ ከቃሊቲ እሥር ቤት ከተፈቱ በኋላ እንደገና መታሰራቸዉ ይታወሳል። በቅርቡ ደግሞ አቶ መስፋን ነጋሽ የአዲስ ነገር ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ፣ እንዲታሰሩ መደረጉ በሰፊዉ እየተዘገባ ነዉ።

  ይህ አይነቱ አካሄድ የሜዲያን ነጻነት የሚጋፋ ዞሮ ዞሮ በኢሕአዴግ ላይ ችግር የሚያመጣ  ነዉ ብዬ አስባለሁኝ። በቶሎ ማስተካከያ መደረግ አለበት።

- የፖለቲካ ድርጅቶች አለ ገደብ እንዲቀሳቀሱ ያስፈልጋል። እንደ አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ የመሳሰሉ ድርጅቶች አለ አንዳች አፈና በኢትዮጵያ ዉስጥ ባሉ ግዛቶች ሁሉ መንቀሳቀስ ከቻሉ፣ በምርጫ 2002 የተሻለ ዉጤት አስመዝግበዉ መንግስት የመመስረት እድል ሊያገኙ እንደሚችሉ እርግጥ ነዉ። ይህ በኢሕአዴግ እንደ ሽንፈት ሊቆጠር ይችላል። ነገር ግን በሽንፈቱ ኢሕአዴግ ያሸንፋል። ይህንን እኔ እንደ ድል ነዉ የምቆጥረዉ። አለአንዳች ማቅማማት ኢሕአደግ ለሚቀጠለዉ ለ 2007 ጠንካራ ተቃዋሚ ሆኖ እንዲወጣ የሚያደርገዉ ሲሆን የኢሕአዴግ ጠንካራ ሆኖ መቀጠል ደግሞ ለአገራችን የዲሞክራሲ ሂዳት በጣም አስፈላጊ ይሆናል።

**የኢሕአዴግ የሕዝብ ግንኙነት ችግር**

«ከፍትፍቱ ፊቱ» እንደሚባለዉ የኢሕአደግ መሪዎች የፈለገዉን መልካም ነገር ቢያደርጉም አብዛኞቹ በቴሌቭዥንና ሬዲዮ በሚቀርቡበት ጊዜ ከአንደበታቸዉ የሚወጣዉ አላስፈላጊ ቃላት ትዕቢት እንደሞላባቸዉ ጥጋበኞች ተደርገዉ እንዲታዩ አድርጓቸዋል። የትም አገር "ትሁት ያልሆነ መሪ" የተጠላ ነዉ። በዚህ ረገድ ኢሕአዴግ ትልቅ ለውጥ ማምጣት ይኖርበታል ብዬ አስባለሁኝ።

በስነ ምግባራቸዉና በሚናገሩት ንግግሮች በሕዝብ ዘንድ የተጠሉ የአመራር አባላትን ኢሕአዴግ ማራቅ አለበት። **እነዚህ ግለሰቦች ፓርቲዉን ወክለዉ እንዲናገሩ መደረግ የለበትም። በተቻለ መጠን የሚናገሩትን የሚያዉቁ፣ ትሁት የሆኑ፣ ጨዋነት የተሞላበት ኢትዮጵያዊ የንግግር ዘይቤ የተካናቸዉና ሕዝብን የሚያከብሩና በሰዎች ዘንድ አንጻራዊ ተቀባይነት ያላቸዉ ሰዎችን በሕዝብ ፊት ማቅረብ ተገቢ ይመስለኛል።** ለምሳሌ እነ አቶ አርከበ እቁባይ፣  የቀድሞ አንጋፋ የአዲስ አበባ ከንቲባ፣ በምርጫ ዘጠና ሰባት ወቅት በተደረጉት ክርክሮች ኢሕአዴግን ወክለዉ ከቀረቡት መካከል አንዱ የነበሩና «ኢሕአዴግም ሰዎች አሉት« ያስባሉት አቶ ግርማ ብሩ የመሳሰሉትን የበለጠ በሕዝብ ፊት እንዲወጡ ኢሕአዴግ ቢያደርግ ጥቅም የሚያገኝ ይመስለኛል።

**የሶማሊያዉ ጦርነት**

በሚያስዝን መልኩ አገራችን ኢትዮጵያ ሳትወረር የኢትዮጵያ ወታደር በሶማሊያ መዝመቱ ኢሕአዴግ ከሰራቸዉ ትልቅ ስህተቶች መካከል ሌላዉ ነዉ። ነገር ግን ይህን  ስህተት ወደ መልካም ኢሕአዴግ ሊቀይረዉ ይችላል ብዬ አስባለሁኝ።

ሶማሊያ ባለዉ የጊዚያዊ መንግስት ዘንድ ኢሕአደግ ተሰሚነት አለዉ። (እንደዉም አለኢትዮጵያ ወታደር በሶማሊያ ያለዉ መንግስት የትም አይደርስም) ስለዚህም በጅቡቲ በቅርቡ የተፈረመዉ የሰላም ስምምነት ዉጤት እንዲያመጣ ማድረግ የሚቻልበት ሆኔታ ላይ ትልቅ ትኩረት ኢሕአዴግ ቢሰጠዉ፣ እነ ሼክ ሸሪፍና እነ ፕሬዘዳንት ሁሴን በጋራ የጥምር መንግስት እንዲመሰርቱና ደቡብ ሶማሊያ እንድተረጋጋ ቢደረግና የኢትዮጵያ ወታደር ሙሉ ለሙሉ ከሶማሊያ ቢለቅ ለኢሕአደግ ትልቅ የፖለቲካ ድል ይሆንለታል ብዬ አስባለሁ።

በአካባቢዉ ሰለምና መረጋጋት ከመጣ ደግሞ ኪሲማዮንና ሞጋዶሾን የመሳሰሉ የሶማሊይ ታላላቅ ወደቦችን መጠቀም የሚቻልበትን ሁኔታ መፍጠር ይቻላል። ይህ ደግሞ ኢሕአዴግ በሶማሊያ ላለዉ ለዘመናት ለቆየዉ ዉዝግብ ዘለቄታዊ መፍትሄ ከማስገኘቱም ባሻገር በደቡብና

በምስራቁ የአገራችን ክፍል የሚኖረዉ ሕዝባችን ከጦርነትና ከረሃብ ነጻ የሚወጣበትንና በልማት የሚያድግበትን ሁኔታ ያመቻቻል። ይህም ኢሕአዴግ በኢትዮጵያ ሕዝብና በታሪክ ዘንድ ትልቅ ቦታ የሚያሰጠዉ ነዉ።

**ለሱዳን ተሰጠ ስለተባለዉ የኢትዮጵያ ግዛት**

ከላይ ከተጠቀሱት ጋር የሚዛመድ ሌላ ችግር ኢሕአዴግ ያለበት“ብሄራዊ ስሜት” እንደሌለዉ ተደርጎ መቆጠሩ ነዉ። ይህንንም ካባባሱት ጉዳዮች አንዱ በቅርቡ በጎንደር አካባቢ ለምለም የሆነን የኢትዮጵያ መሬት ለሱዳን ተሰጠ የተባለዉ ጉዳይ ነዉ።

ይህ ጉዳይ በሚስጥር መያዙ፣ ከጥንስሱ ፓርላማ እንዲያወቀዉ አለመደረጉ፣ ነገሩ ገሃድ ሲወጣ ደግሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት መካዱ፣ ከዚያም አሳማኝ ያልሆነ ማስተባበያ በመስጠት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፓርላማ ለማስረዳት የሞከሩት ሁሉ ኢሕአደግን ጎድቶታል። አሁንም እየጎዳዉ ነዉ።

ይልቅ ኢሕአደግን የምመክረዉ ቢኖር ባለሞያዎችን ያቀፈ ገለልተኛ ኮሚሽን በቶሎ እንዲያቋቁም፣ ኮምሽኑ ደግሞ በቦታዉ ተገኝቶች ሳይንሳዊ የሆነና የተጨበጠ ማስረጃ እንዲሰበስብና ለሕዝብ ይፋ እንዲያደርግ ቢያደርግ ነዉ። በዚህም ሂደት በኢሕአደግ ዘንድ ስህተቶች ከተሰሩ በአስቸኳይ እርማት እንዲደረግባቸዉ ከተደረገ በቀላሉ በሱዳን ድንበር ጉዳይ የሚደርስበትን ትችት ዝም ማሰኘት ይችላል።

ጽሁፌን ከማጠቃለሌ በፊት ኢሕአዴግን ስለመቃወሜና አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲን ስለመደገፌ ሁኔታ ልመለስ። መቃወሜ ወይንም መደገፌ በመርህና በፖለቲካ ፕሮግራማቸዉ ላይ በመመስረት ነዉ። ስለዚህ ኢሕአዴግ ኢትዮጵያዊነትን ካንጸባረቀ፣ በጡንቻ የመተማመን ፖለቲካዉን ከተወ፣ ከላይ እንደዘረዘርኩት መሰረታዊ ማሻሻያዎችን ካደረገ አሁን ብንቃወመዉም ነጋ ልንደግፈዉ እንችል ይሆናል።

የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እምነት ሊኖራቸዉ ይገባል። ሕዝቡን መፍራት ማቆም አለባቸዉ። እዉነተኛ ሆነዉ ከተንቀሳቀሱ፣ በእነርሱና በህዝቡ መካከል ያለዉን ችግር ካስወገዱ የኢትዮጵያ ህዝብ እንደገና እድል ሊሰጣቸዉ ይችላል ብዬ አስባለሁኝ።

አብዛኛዉ ኢትዮጵያዊ ታማኝነቱ ለፖለቲካ ድርጅት ሳይሆን ለአገሩ ነዉ። ነገ ኢሕአዴግ በትህተና መንፈስ ጥሩ አማራጮችን ካቀረበ የሚሰማ ጆሮ የኢትዮጵያ ህዝብ አለዉ።